# አዳም ረታ እና የኤግዚቴንሻሊዝም ፍልስፍና

መኮንን ማንደፍሮ

በምዕራባዊያን የፍልስፍና ታሪክ ውስጥ እንደ ኤግዚቴንሻሊዝም (existentialism) በኪነ-ጥበባዊ ሥራዎች ላይና በግለሰባዊ የአኗኗር ባህል ላይ ታላቅ ተፅእኖን የፈጠረ ፍልስፍና የለም፡፡ የእዚህ ፍልስፍና ዋና የጥናት ትኩረት የሰው ልጅ ነው፡፡ በመሠረታዊነትም ግለሰብን ማዕከል አድርጐ በህልውና ውስጥ ያሉ ነባራዊ ሁኔታዎችን ያጠናል፡፡

የኤግዚቴንሻሊዝም ፍልስፍና የተነሳው በዋናነት የተፈጥሮአዊነትን (naturalism) እና የሐሳባዊነትን (idealism) ሜታፊዚካል መርህ በመቃወም ሲሆን ከፍሬዲሪክ ሺለር የሰብአዊነት (humanism) ፍልስፍናዊ እሳቤ ጋር ተቀራራቢነት አለው፡፡

ኤግዚቴንሻሊዝም የምዕራባውያን ፍልስፍና የቆመበትን የስፔኩሌቲቭ ፍልስፍና (speculative philosophy) የሚተች የፍልስፍና ፅንፍ ሲሆን የእዚህ አይነቱ ፍልስፍና ዐቢይ ትኩረት ከነባራዊ የሰው ልጅ ህላዌ መሠረታዊ ተግዳሮቶች እጅግ የራቀ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ እንደ ኤግዚቴንሻሊስቶች አመለካከት የፍልስፍና መሠረታዊ አላማና ትኩረት የሰውን ልጅ ማዕከል ያደረገ መሆን ይገባዋል፡፡ ፍልስፍናው ከጥንታዊያኑ ታላላቅ የግሪክ ፈላሥፎች ጀምሮ እስከ መካከለኛው ዘመን ድረስ የዘለቀ ታሪካዊ መሠረት ያለው ሲሆን ይበልጥ ገናና የሆነው ግን በሃያኛው ክፍለ ዘመን ነው፡፡

ኤግዚቴንሻሊዝም የጥናት ትኩረቱን በዋናነት ያደረገባቸው ብዙ ርእስ ጉዳዮች ሲኖሩ ከእነዚህ መካከል ስለ ሰው ልጅ የነፃነት ወሰን (freedom)፣ ግለሰባዊ ኃላፊነት (responsibility) ቋሚና ተፈጥሮአዊ የሆነ ሰብአዊ ማንነት (መገለጫ ባሕርይ) አለመኖር (the nonexistence of fixed human essence)፣ ሞት (death)፣ እውነተኛነት (authenticity)፣ ብቸኝነት (lonliness) እኩይ ሥነ-ልቦናዊ አመለካከት (bad faith)፣ ስለ ህልውና ትርጉም አልባነት (absurdity)፣ ከግለሰባዊ ማንነት በፊት ህልውና እንደሚቀድም (existence precedes essence)፣ ቀቢፀ-ተስፋ (despair)፣ ባይተዋርነት (strangeness)፣ ጭንቀት (anguish)፣ ከግለሰብ አቅምና ነፃ ፈቃድ ውጪ የሆነ ግለሰባዊ ማንነትንና ሁኔታን የመወሰን ሥልጣን ያለው አካል አለመኖር (the nonexistence of determinism) እና ሌሎች ርእሰ ጉዳዮች ላይ ያተኩራል፡፡

የዚህ ጽሑፍ ዋና አላማ በዘመናዊው የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍ (contemporary Amharic literature) ላይ ዐቢይ ተፅእኖውን ባሳደረው ታላቁ ደራሲ አዳም ረታ የፈጠራ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ የሚገኙትን መሠረታዊ የኤግዚቴንሻሊዝም ፍልስፍና ፅንሰ- ሐሳቦች መዳሰስ ነው፡፡

አዳም ረታ ዘመናዊውን የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍ ረጅም ርቀት ያሻገረ፣ ተለምዶአዊውን የልብወለድ ድርሰት አጻጻፍ አካዳሚያዊ ሕግ የሻረ፣ በምትኩም አዳዲስ የአጻጻፍ ዘይቤዎችን ያስተዋወቀ ታዋቂ ደራሲ ነው፡፡ የፈጠራ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎቹ ከብዙ አካዳሚያዊ የጥናት መስኮች (interdisciplinary) አንግል መተንተን የሚችሉ ናቸው፡፡ ሥራዎቹ ፍልስፍናዊ እሳቤዎችን (philosophical thoughts)፣ ሥነ-ማህበረሰባዊ ጉዳዮችን (sociological subjects)፣ ታሪክን (history)፣ ሠብአዊ ሥነ-ልቦናዊ ጉዳዮችን

(psychological subjects)፣ ኃይማኖትን (religion) እና ፖለቲካን (politics) በዋናነት አጠቃለው የያዙ ናቸው፡፡
የአዳም የፈጠራ ሥራዎች ኢትዮጵያዊነት የሚፈተሽባቸውን አጠቃላይ ህልውናዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ገፀ-ባሕርያቱን መሠረት አድርገው ከታሪክ፣ ከባህል፣ ከሥነ-ልቦናና ከፖለቲካ አንፃር ያስቃኙናል፡፡ እነዚህን አጠቃላይ ህልውናዊ ነባራዊ ሁኔታዎች የሚፈተሽባቸውን መንገዶች ተከትለን ከምዕራባዊያን በተወረሰ ማንነት፣ የዕውቀትና የእምነት የአስተሳሰብ መሠረት (eurocentrism) እና የኢትዮጵያዊነት አሻራ የሚንፀባረቅበት አጠቃላይ የህላዌ ርዕዮተ- ዓላም (ethiocentrism) መካከል ያለውን ልዩነትና ግጭት እንረዳለን፡፡ የኢትዮጵያዊነት አሻራ የሚንፀባረቅበት የህላዌ ርዕዮተ-ዓለም (ethiocentric world view) በገፀ- ባሕርያቱ ግላዊ ሥነ- ልቦናዊ ሁኔታዎች፣ ሥነ -ማህበራዊ ትስስሮችና ኃይማኖታዊ እሳቤዎች አማካኝነት ተገልፀው ይገኛሉ፡፡

የፍልስፍናን እና የሥነ -ጽሑፍን ጥብቅ ቁርኝት ተከትሎ ፈላስፋው በደራሲው ሥራ ላይ ወይም ደራሲው በፈላስፋው እሳቤ ላይ ተፅእኖን የማሳደሩ ሐቅ ተለምዶአዊ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የተለያዩ የኤግዚቴንሻሊዝም ፍልስፍና ፅንሰ- ሐሳቦችን በአዳም ረታ የፈጠራ የድርሰት ሥራዎች ውስጥ እናገኛለን፡፡

ኤግዚቴንሻሊዝም የሰው ልጅ ህልውና ከማንነቱ መገለጫ ባሕሪው ይቀድማል (existence precedes essence) የሚለውን ሜታፊዚካዊ መርህ (metaphysical doctrine) አፅንኦት ሰጥቶ የሚሰብክ ፍልስፍና ሲሆን ቀደም ብሎ በብዙ ፈላስፎች ትምህርት ውስጥ ትልቅ ቦታ የነበረውን የሰው ልጅ ማንነት መገለጫ ባሕርይ ከህልውናው ይቀድማል (essence precedes existence) የሚለውን የኢሴንሻሊዝም (essentialism) ሜታፊዚካዊ አመለካከት ይቃረናል፡፡ ታዋቂዎቹ የግሪክ ፈላስፎች ፕሌቶና አሪስቶትል የእዚህ ሜታፊዚካዊ እሳቤ ዋና አራማጆች ናቸው፡፡ ፕሌቶ በዚህ ዓለም ያለው ነገር ሁሉ ቋሚ (ዘላለማዊ) የሆነ መገለጫ ባሕርይ (eternal essence) አለው ብሎ የምናል፡፡ ለኤግዚቴንሻሊዝም ፍልስፍና አራማጆች ይህ አይነቱ እሳቤ ፍፁም ስህተት ነው፡፡ እንደ ሳርተር አመለካከት የሰው ልጅ እንደ ግኡዛን ቁሳዊ ነገሮች (nonconscious corporeal beings) ሊለወጥ የማይችል ቋሚ የሆነ ተፈጥሮአዊና ታሪካዊ ማንነት (መገለጫ ባሕርይ) የለውም፤ ነገር ግን ግለሰቡ በራሱ ምርጫና ኃላፊነት ማንነቱን ይፈጥራል፡፡ በእዚህም አቅሙ ጠቅላላ ነባራዊ ሁኔታዊን ሳይገነዘብ በፊት ተቀብሎት ከነበረው (ማህበረሰቡ ከሰጠው) የማንነት መገለጫ ወጥቶ አዲስ ማንነትን መላበስ ይችላል፡፡ ይህን አመለካከት ማርቲን ሃይዲገርም ይደግፈዋል፡፡ እንደ ሃይዲገር እሳቤ የጥንታዊው ፍልስፍና ዐቢይ ሜተፊዚካዊ ችግር የሰው ልጅ ወደ ህልውና ከመምጣቱ በፊት በተፈጥሮ የሰጠው ቋሚ የሆነ ማንነትና መገለጫ ባሕርይ እንዳለው አድርጐ ማቅረቡ ነው፡፡ በተቃራኒው የሰው ልጅ የማይለወጥ ተፈጥሮዓዊ ማንነት (fixed human essence) የለውም፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በአዳም የልብወለድ ሥራዎች ውስጥ የሚገኙት ገፀ-ባሕርያት የቀደመ ታሪካዊና ሥነ-ልቦናዊ ማንነታቸውን (essence) ቀይረው አዲስ ሥብዕናን ሲላበሱና አዲስ ኑሮን ሲመሠርቱ እናገኛቸዋለን፡ ፡ ለእዚህ ማሳያ የሚሆነን በደራሲው ተጠቃሽ መፅሐፍ አለንጋና ምስር የአጭር ልብወለድ ስብስብ ሥራ ውስጥ ኦቾሎኒ በተሰኘው ትረካ ውስጥ የሚገኘው ዋና ገፀ - ባሕርይ ስምኦን ነው፡፡ ስምኦን በእኩይ ሥነ- ልቦናዊ እምነት (bad faith) ውስጥ እያለ ማህበረሰቡ የሰጠውን መገለጫ (የመልኩን አስቀያሚነት) አምኖ ተቀብሎ በማንነቱ የሚሸማቀቅ፣ በራስ መተማመኑ የተሸረሸረ ግለሰብ ነበር፡፡

"... እድሜየ አሥራ አራት እስኪደርስ በመልኬ እሰደብ ነበር (በኋላም ቀረልኝ ማለት ሳይሆን)፡፡ እኔም ተጨባጭ መረጃ ይገኔ ከመከራከር ይልቅ የተባልኩትን በመስማት፣ ሰምቼም በማመን ዝቅተኛነት የወረረኝ፣ አስቀያሚ የተባለ ፊቴን ሰው ፊት በኩራትና በራስ መተማመን ማሳየት የሚከብደኝ ነበርኩ፡፡ የሥነ ልቦና በሽታ በሉት ብትፈልጉ... 'አስቀያሚ' ተብዬ መሰየሜ የፈጠረብኝን አጥንቴ ድረስ የተጠለለውን የውርደት ስሜት፡፡ ይኼን ፕሮፓጋንዳ የትኛው ጐረቤቴ ወይም የቤተሰብ አባል አውጥቶልኝ አምኜ ተከትየው እኔን የወጣትነት ጨለማ ውስጥ እንደከተተኝ አላውቅም፡፡ የማውቀው ማፈሬን ነው (አዳም፣ 2004፡ 232-233) ፡፡"

"... በተለያየ ቴክኒክ፣ ባልገባኝ ብልጠትም የማላውቃቸውና የማያውቁኝ ሰዎች የሰሩኝ ቅኝ ግዛት ነበርኩ" (አዳም፣ 2004፡ 239) ፡፡

እዚህ ታሪክ ውስጥ ስምኦን ግላዊ ሕይወቱን ለመቀየር ያለውን ነፃነትና ሚና በመረዳትና ኃላፊነቱን በመውሰድ ከእኩይ እሳቤ (bad faith) መጥቶ ማንነቱን በመለወጥ ማድረግ ይፈልግ የነበረውን ነገሮች ሲያሳካ እናያለን፡፡ በታሪክ ውስጥ የተገለፀችው ሴት በፍቅር መማረኩና ከሌሎች ብዙ ሴቶች ጋር ፆታዊ ግንኙነትን መፍጠር መቻሉ የዚህ ጥረቱና ስኬቱ አንዱ ማሳያ ነው፡፡

"... ያኔውኑ ከሲኒማ ቤት ወጥቼ የሆነ መአት ሕዝብ በሚመላለስበት ቡና ቤት፣ መአት ሕዝብ ባለበት... ሴትና ወንድ... ማንም ፊት ለፊት እንድታይ ሆኘ መቀመጥ ፈለግሁ፡፡ በአስጠላችኝ፣ በጠላችኝ የከተማየ መንገዶች መጓዝ ፈለግኩ፡፡ እያፏጨሁ፣ እየዘፈንኩ" (አዳም፣ 2004፡ 239) ፡፡

"... በጐዳናዎች፣ በከተማው የሚታይ ሎጋ ሆኘ ወጣሁ፡፡ ... እና እየቆየ በራስ መተማመኔ እያደገ ሌላ ሴት እንደሚፈልገኝ፣ እንደሚያየኝ ስረዳ ትሰለቸኝ ጀመር፡፡ ... እኔ በተገኘው ክፍት ቦታ ሌሎች ሴቶችን ማማለል ወጣሁ፡፡ ብዙ ቀላቀልኩ፡፡ ቀድሞ ችላ የሚሉኝ የሚመስለኝን ደፈርኩ" (አዳም፣ 2004፡ 241) ፡፡

ግለሰባዊ ነፃነት (freedom of the subject) ሌላኛው ዐቢይ የኤግዚቴንሻሊዝም ፍልስፍና መገለጫ ነው፡፡ እንደ ሳርተር እሳቤ እያንዳንዱ ግለሰብ መሆን የሚመኘውን ለመሆን ፍፁም ነፃነት ያለው ሲሆን ይህ ነፃነቱም ሊሸሸው የማይችል ሐቅ ነው፡፡ እንደ እሱ እምነት ሰው ነፃ አለመሆን አይችልም፤ ምክንያቱም ነፃ እንዲሆን ተፈርዶበታል፡፡

እያንዳንዱ ግለሰብ ለገዛ ህልውናው ኃላፊና ጌታ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ግለሰቡ የራሱ እግዜር ነው፡፡ በሕይወቱ አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታና ዕጣ ፈንታ ላይ እግዜር፣ ተፈጥሮና ማህበረሰብ አንዳችም ተፅዕኖና ሚና የላቸውም፤ ግለሰቡ ይህን ግላዊ ሥልጣን በእኩይ እሳቤ (bad faith) ወድቆ ለእነዚህ አካላት አሳልፎ ካልሰጠ በቀር፡፡ ለግላዊ ኑሮ ነባራዊ ሁኔታ እነዚህን ውጫዊ አካላት ተጠያቂና ባለሙሉ ሥልጣን አድርጐ መቀበል ራስን መዋሸት (self deception) እንደሆነ ሳርተር ይገልፃል፡፡

በኤግዚቴንሻሊዝም ፍልስፍና አራማጅ ፈላስፎች ግላዊ ሕይወትና በፈጠራ የሥነ - ጽሑፍ ሥራዎቻቸው ውስጥ በሚገኙት ዋና ገፀ- ባሕርያት ውስጥ ማህበራዊ ገዥ እሴቶችን (societal moral sanctions) የመቃወምና የመጣስ የሞራል አፈንጋጭነት (deviation) ተንፀባርቆ ይገኛል፡፡ የእዚህ አመፅ ዋና ግብ ግላዊ ነፃነትን መቀዳጀት ነው፡፡ ይህ አይነቱ ሁኔታ በአዳም የልብወለድ ሥራዎች ወስጥ በሚገኙት ገፀ- ባሕርያት ላይም በዋናነት የሚስተዋል ነው፡፡ የአዳም ገፀ- ባሕርያት ግላዊ ነፃነትን ፍለጋ ማህበረሰቡ የደነገገውን ጥብቅ

ወግና ሥርአት ሲነቅሱ ይታያል፡፡ ይህ የገፀ - ባሕርያቱ እምቢተኝነት የሚስተዋለው ማህበረሰቡና ኃይማኖት ካበጀው ሕግ ባሻገር በራሳቸው እውነት፣ የሞራል እሴትና የህላዌ ትርጉም መኖርን የመምረጥ ዝንባሌ ውስጥ ነው፡፡
ለሳርተር ይህ አይነቱ ግላዊ የአኗኗር ሁኔታ ትክክለኛ (authentic existence) ነው፡፡ ከሰማይ የወረደ ፍርፍር በተሰኘው የአጭር ልብወለዶች ስብስብ ውስጥ ሁለት ልጃገረዶች በተሰኘው የደራሲው ታሪክ ውስጥ የተገለፀው ዋና ገፀ- ባሕርይ ከላይ የተገለፁት የኤግዚቴንሻሊዝም ፍልስፍና መገለጫ የሆኑ የግለሰብ ግላዊ ባሕርያት ይንፀባረቁበታል፡፡

"... በሕይወቴ ወጥ ውስጥ ትንንሽ የእብደት ቅርንፉድ፣ የልክስክስነት ኮረሪማ፣ የባለጌነት ነጭ ሽንኩርት፣ የደደብነት ጥቁር አዝሙድ...የመሳሰለ ልጨምርበት እፈልጋለሁ፡፡ እነዚህ ቅመሞች ያሉበትን ሐጢያታዊ ማታና ምሽት ከሰዎች ጋር ልኖራት ግን አልፈልግም፡፡ ይህቺን አይነት እብደት ከሚያውቁት ሰው ጋር ሆነው ሲኖሯት ትቀጥናለች፡፡ ትዕዝብት፣ ትቺት፣ 'ይቅርብህ' 'ጥሩ አይደለም' 'ይደብራል' የተሰኙ ቃላቶችና የሚከስቱዋቸው ስሜቶች ይወረወሩብኛል፡፡ በቂ ነፃነት የለውም፡፡ ያቺ የእብደት ቀኔ የእኔ ጦር ሜዳ ናት፡፡ ፊታውራሪ እኔ፣ ተራ ወታደር እኔ፡፡ አዛዥ እኔ ነኝ ታዛዥ እኔ" (አዳም፣ 2002፡97)፡፡

ዋና ገፀ -ባሕሪው በማህበራዊ የኑሮ ደረጃው ከከፍተኛው የህብረተሰብ መደብ (ከጨዋውና ከተከበረው) የወጣ ነው፡፡ በመሆኑም ካለው ማህበራዊ ደረጃ አንፃር ህብረተሰቡ ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸውን ማህበራዊ ወጐችና ኃይማኖታዊ እሴቶች በአኗኗሩ እንዲተገብር ይጠበቃል። በተቀራኒው የገፀ- ባሕሪው ድርጊቶች ግን የማህበረሰቡን እሴቶች የሚቀናቀኑ አፍራሽ ናቸው፡፡ ለአንድ የእዚህ ህብረተሰብ አባል ዋና ገፀ- ባሕሪው ማህበረሰቡ ከፍተኛ ቦታ ከሚሰጣቸው የመሳፍንት ወገን የወጣ መሆኑን ቢረዳ ድርጊቶቹ ፍፁም እንግዳ ይሆኑበታል፡፡ የገፀ-ባሕሪው ድርጊቶች በማህበረሰቡ የእሴት ሚዛን ቢዳኙ የግለሰቡን ማህበራዊ ክብርና ደረጃ (societal privileged status) ስለማያንፀባርቁ የሚወገዙ ናቸው፡፡ በታሪኩ ውስጥ ገፀ- ባሕሪው የማህበረሰቡ ጨቋኝ ወግና ሥርአት ሳይገድበው ውስጣዊ ፍላጐቱን ለማሳካት ትክክለኛ ናቸው ብሎ የአመነባቸውን ድርጊቶች ሲያደርግ እናገኘዋለን፡፡ የእዚህ አንዱ ማሳያ ኒኒ ከተባለች ሴተኛ አዳሪ (prostitute woman) ጋር የሚመሠርተው ግንኙነት ነው፡፡

"... ሃያ ብር አውጥቼ ሰጠኋትና የቀረውን እንድትይዘው ነገርኳት፡፡ ልብሷን አወለቀች፡፡ ጡቶቿ ድንኳን በሚያሳፍር መያዣዎች ተይዘዋል፡፡ ወገቧ ቢቀጥንም አጭር ነው ... ወደ ፊኛዋ አካባቢ ቦርጭ ይሁን ምን ስሙን የማላውቀው ሥጋ አለ፡፡ እግሮቿ አጫጭሮች ናቸው፡፡ አልጋ ውስጥ ገባች፡፡ ኮቴንና ሱሪዬን አወለቅኩና ተከተልኳት" (አዳም፣ 2005፡ 102) ፡፡

በ ገፀ-ባሕሪው ድርጊቶች ውስጥ የተገለፀው ግላዊ ባሕርይ ነፃነትን ለማረጋገጥና ራስህን በመሆን ሂደት ውስጥ የሚገኝን ደስታ ለማግኘት እያንዳንዱ ግለሰብ የሚወስደው ውሳኔ ማሳያ ነው፡፡ ስለሆነም ገፀ- ባሕሪው የማህበረሰቡን የሥነ- ምግባር እሴት ቸል በማለት ግላዊ ነፍሱን ለማስደሰት በመጠጥ ሲሰክር ይታያል፡፡

"...በመጀመሪያ የማደርገው ነገር የለገደብ መጠጣት ነው፡፡ ቢራ ሳይሆን ጂንና ብራንዲ" (አዳም ፣2002፡ 99)

የአዳም 'አለንጋና ምስር' መጽሐፍ ከሌሎቹ የሥነ-ጽሑፍ ሥራወቹ በአንጻራዊነት በዛ ያሉ የኤግዚቴንሻሊዝም ፍልስፍና ዐቢይ ርእሰ ጉዳዮች ተዳሰው የቀረቡበት ነው፡፡ የሰው ልጅ ህልውና አሰልቺነት (አሰልቺነቱ በዘወትራዊ ተመሳሳይና ተደጋጋሚ የሕይወት ጉዞ ምክንያት የተከሰተ ስሜት ነው) እና ትርጉም አልባነት (the absurdity of existence) መጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙ ዐቢይ ፅንሰ-ሐሳቦች አንዱ ነው፡፡

ይህ ፅንሰ-ሐሳብ በአልበርት ካሙ የፍልስፍና እና የስነ-ጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ በጥልቀት ተዳሷል፡፡ እንደ ካሙ እሳቤ ፍፁም በሆነ መንገድ የሕይወትን ትርጉም መፍጠር የሚችልና የሰው ልጅን የትርጉም አልባነት ስሜት ሊያጠፋ የሚችል (ሃይማኖትን፤ሳይንስን እና ፍልስፍናን ጨምሮ) አስተምህሮ የለም፡፡ ምክንያቱም ሕልውና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ሊገለፅ የሚችል ትርጉም ወይም አላማ ፈፅሞ የለውም፡፡ ከሰው ልጅ እሳቤ በተቃራኒው አለሙ ቋሚ የሆነ ሕግና ስርዓትን ተከትሎ የሚተዳደር አይደለም ፣ ከሰው ልጅ ጋርም ሕብረት የለውም፡፡ የሰው ልጅ የሕልውና አላማና ትርጉም ራሱ ግለሰቡ የሚፈጥረው እንጂ ተፈጥሮአዊ መሰረት ያለው አይደለም፡፡ የሕይወት ትርጉም የሚጀምረው የሰው ልጅ በሚኖርበት ትርጉም አልባና አላማ ቢስ ዓለም ውስጥ ራሱ በመረጠው መንገድ ግላዊ ትርጉምን ፈጥሮ መኖር እንደሚችል ሲገነዘብና ሲወስን ነው፡፡

የህልውና ትርጉም አልባነት ስሜት የሚፈጠረው እንደ ካሙ አመለካከት የሰው ልጅ በሕይወቱ ውስጥ ሁል ጊዜ ደስታን፤ ሰላምን አንድነትንና መረጋጋትን ስለሚፈልግና ምክንያቱ በማይታወቅ መልኩ የእነዚህም ነገሮች ተቃራኒ ዓለሙ ስለሚለግሰው ነው፡፡ ምክንያቱም ዓለሙ ከሰው ልጅ ግብ፣ አለማና ምኞት ጋር ሕብረት እንዲፈጥር የሚያደርግን ስርአት አይከተልም፣ ለሰው ልጅ ዘወትራዊ ፍላጐት፣ ምኞትና መከራ ባዳና ግድየለሽ (indifferent) ነው፡፡ እንደ ካሙ እሳቤ የሕይወት ከንቱነት ስሜት ፍፁም የተገለጠ ሐቅ ነው፡፡

ይህ የኤግዚቴንሻሊዝም ፍልስፍና ፅንሰ-ሐሳብ 'ያ ሐመልማል' በተሰኘው የአጭር ልብወለድ ታሪክ ውስጥ ዋና ጭብጥ ሆኖ ቀርቧል፡፡ እዚህ ታሪክ ውስጥ በአንድ ባልተጠበቀ አጋጣሚ እጅግ ታፈቅረው የነበረውን ባሏን በሞት በማጣቷ ብቸኝነት ከቧት ቀቢፀ-ተስፋ የነገሰበት ሕይወትን የምትገፋ ገፀ-ባሕሪ እናገኛለን፡፡ በገፀ-ባሕሪዋ ባል ሕይወት ውስጥ የተፈጠረው ያልተጠበቀ አሳዛኝ ክንዋኔ (የክንዋኔው አሳዛኝነት ከሰው ልጅ አቀባበልና ልምድ አንፃር ነው) በሰው ልጅ የምክንያታዊነት አረዳድ አቅም ሊገነዘቡትና ለምን እንደሆነ ትንታኔ ሊቀርብበት የሚችል አይደለም፡፡ ይህ ክንዋኔ የሰው ልጅ ነባራዊ ህልውናዊ ሁኔታ ቁልጭ አድርጐ ያሳያል፡፡ "... በዓለም ላይ አንድ ሰው ብቻ ተወዶ ያም አንድ ሰው ሲሞት ምን ይደረጋል? ቤት ለብቻው ምን ትርጉም አለው? ዛሬ ማታ ብቻየን ከምኖርበት ስሙ የተጠራ ግዙፍ ቤት ሳሎን ውስጥ በባለ መስታወቱ ሠፊ በር በኩል ወደ ውጪ አያለሁ ... ያረጁ የፀደይና የአብዘርቨር መፅሔቶች ከባሌ ጋር አብረን የምናነባቸው የነበሩ... የምንስቅባቸው፣ የምንወያይባቸው ... እነሱን ዛሬ ደግሜ ደጋግሜ አንብቤ አዳክመውኝ፣ ሰልችተውኝ፣ አንዳንዴም አማረውኝ እንደ አጋጠመኝ ወርውሬአቸው የወለሉ ከፊል በተገላለጠና በተከደነ እነሱ ተሸፍኖአል" (አዳም፣ አለንጋና ምስር፣2004፣ገፅ 252) ፡፡

"... ዛሬ እዚህ ሳሎ ተቀምጬ ... ወደ ውጭ ስመለከት... የእኔ ሕይወት አጠወላለጉ እስኪያስደነግጠኝ፣ እስኪያሳብደኝ ድረስ ተዘበራርቆና ወድቆ ሳለ እዛች አጥሬ ዙሪያ የተንጠለጠለው የሐረግ አትክልት ሐመልማሉ ግን አማረም አላማረም ሳያቋርጥ መድመቁ፣ መተንፈሱ ይገርመኛል"
(አዳም፣ አለንጋና ምስር ፣2004፣ ገፅ 258) ፡፡

ዓለሙ ውስጥ የሚከናወኑና የሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ የሚፈጠሩ ነገሮች ለምን እንደተከናወኑ በምን ዓይነት ሂደት እንደሚከናወኑ... ወዘተ ምክንያታዊ የሆነ ትንታኔ ሊቀርብላቸው ስለማይችል የሰው ልጅ ህልውና ዓለማ ቢስና ማብቂያ በሌለው የድግግሞሽ ሕግ የተሞላ (pointless) ነው፡፡ ግለሰቡ ይህን ድግግሞሽ ሲያስተውል የመሰልቸትና ተስፋ የሞቁረጥ ስሜት ይፈጠርበታል፡፡

የሰው ልጅ በአጠቃለይ ህልውናዊ ሁኔታው ግራ ማጋባትና ትርጉም ማጣት የሚጀምረው በእሱ ዘወትራዊ አወንታዊ ምኞቱና ከዚህ በተቃራኒው ቸልተኛውና ከእሱ ቅድመ እሳቤ ጋር የሚጣረስ ስርዓት በሚያካሂደው ኢ-ምክንያታዊው ዩኒቨርስ (irrational universe) መካከል የለውን ኢ-መስተጋብራዊ ሁኔታ ሲያስተውል ነው፡፡ ይህ ፍልስፍናዊ ፅንሰ- ሐሳብ "ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ" በተሰኘው የአዳም ረታ የስነ-ጽሑፍ ሥራ ውስጥ 'ኩሳንኩስ' በሚለው የአጭር ልብወለድ ታሪክ ውስጥ ተዳሶ ይገኛል፡፡

"... ለረጅም ጊዜ የልተለወጡ ልብሶቼ እላዬ ላይ ይንጀላጀላሉ፡፡ ያን አየሁ፡፡ ሥጋዬ ችኩል ሆነ፡፡ ሴትነቴ ተቅበጠበጠች፡፡ ምን ማለቴ እንደሆነ ይገባችኋል፡፡ የክፍሉ ትዝታ በልታወቁ ኃይሎች እንደ ታዘዘ ሁሉ ከህሊናየ ጀርባ ደብዘዝ ብሎ ቆመ"
(አዳም፣ ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ፣ 2003፣ ገፅ፣ 225)

"... እንዲህ በቀለለኝ ዕለት ነው በመኪና የተገጨሁት፡፡ እንዲህ አንቀዥቅዥኝ የወጣሁ ዕለት ነው አደጋው የደረሰብኝ፡፡ ትልቁ ፖስታ ቤት አካባቢ መንገድ ስሻገር ውይይት ታክሲ ገጨኝ፡፡ አደጋ በይመረጥም ሕይወቴ ግን አላለፈችም፡፡ብዙ አልተጎዳሁም፣ አጥንቴ አልተሰበረም፡፡ የልብ ሞቴ አልቆመም፡፡ ራሥ ቅሌ አልተሰነጠቀም፡፡ መንገድ መሐል ከቆሙት ደሴቶች ዙሪያ ጥቅሙ ያልገባኝ ጨረራም ሽቦ ግን ግራ ዐይኔ ላይ ወጋኝ፡፡ ሆስፒታል ገብቼ ከወጣሁ በአስራ አምስተኛው ቀኔ አንድ ዐይና ሆንኩ" ( ዝኒ ከማሁ)፡፡

ገፀ-ባሕሪዋ በባሏ ሞት ምክንያት ተከስቶባት ከነበረው ቀቢፀ-ተስፋ ካጠላበት ስነ-ልቦናዊ ሁኔታ አገግማ በጉጉት እና በሙሉ ተነሳሽነት አዲስ የሕወቷን ምእራፍ በጀመረችበት ወቅት ነበር ፈፅሞ ምክንያታዊ ምላሽ ልታቀርብለት የማትችለው ያልጠበቀችው አደጋ የደረሰባት ። ክስተቱ የሰው ልጅን ህልውና ትርጉም ኣልባነት የሚያሳይ ነው ።

የሰው ልጅ የህልውናን ትርጉም አልባነት እና ድግግሞሽ መገንዘብ ሲጀምር ጥልቅ የሆነ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ስለሚሰማው አለመኖርን (suicide ) ከዚህ አይነቱ የሰው ልጅ ተጨባጭ ሓቅ ለማምለጥ እንዳማራጭ ሊያቅደው ይችላል ። ለ ካሙ ይህ አይነቱ ተግባር ኢ-ሞራላዊ ስለሆነ የሚወገዝ ነው። ካሙ ለእነዚህ መሰረታዊ ህልውናዊ ተግዳሮች እንደመፍትሄ ያቀረበው ሐሳብ ራሱን ትርጉም አልባነትንና በድግግሞሽ የተሞላ ኑሮን መቀበል (acceptance) ነው። እንደ እሱ እሳቤ የሰው ልጅ ህልውና ትርጉም አልባና አሰልቺ (አሰልቺ የሆነው ተመሳሳይ በመሆኑ ምክንያት ነው) ስለሆነ ከእዚህ ቀውስ ለመውጣት ራስን ማጥፋት ብቸኛ አማራጭ አይደለም፤ ምክንያቱም አንድ ግለሰብ ይህን ህልውናዊ ሐቅ ተቀብሎ  በእዚህ ትርጉም አልባ በሆነ ዓለም ተመሳሳይ ኑሮውን መቀጠል ስለሚችል።

እንደ ካሙ እሳቤ ብቸኛው ትክክለኛ መፍትሄ ይሄ ነው። ይህን መሰረታዊ አሰተምህሮ ተገንዝቦና እንደመመርያ ተቀብሎ በእዚህ ትርጉም አልባ ዓለም ውስጥ ህልውናውን ለመቀጠል የወሰነውን ግለሰብ ጀግና (the absurd hero) ይለዋል ። ይህ ፍልስፍናዊ ርእሰ ጉዳይ ከላይ በተገለፀው የአዳም ስራ ኩሳንኩስ በተሰኘው ታሪክ ውስጥ ይገኛል ።

"… ትንሽ ፊትና የሚያስደነግጥ ትልቅነት ያላቸው ዐይኖች ነበሩኝ። ይሄ ማንም የሚለው ነው። አንዳንድ ጊዜ እንዳውም እጅግ ከማጉላታቸው የተነሳ ‘ዉሮ’ ያስመስልኛል ይሉኛል ። ጠዋት ከእንቅልፌ ስነሳ ዓይኖቼ አይንጮሎጮሉም። ባሌ ከእንቅልፉ እንደባነነ የሚስመው እነዚህን ዓይኖቼን ነበር (አዳም ፤ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ ፤ 2003፤ ገፅ 222) ።

… ታድያ ለመጀመርያ ዕለት ተዋውቀን በሚቀጥለው ቀን ተቃጥረን ስንገናኝ በሚችላት በጣም ትንሽ አማርኛ እና ቀላል ቃላት ዐይኖቼ ትልቅና ዉብ እንደሆኑ ነገረኝ ። ዕንቁ እንደሆኑ ነገረኝ (ዝኒ ከማሁ )።

… ከአስራ አምስት ቀን በፊት በልደታ ዓይን ነበረኝ ። ለኪዳነምህረት አንድ ዓይና ሆንኩ። በፍልስፍናየ የምጠብቀው አደጋ ነው። አዝናለሁ፣ ይከፋኛል ። ግን ምን ይጠበስ? ቁስሉ ሲድን የላስቲክ ዓይን አስገባሁ (አዳም ፤ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ ፤ 2003 ፤ ገፅ 225) ።

… ክፍሉ ከሞተ በኋላ ለሁለተኛ ቀን ዓይኖቼን ስኳል የምኩለው ሁለት የተለያዩ ዐይኖቼን ነው ። ‘የታወረውን እኩላለሁ እንዳትይን ብቻ ’ የሚሉ ይኖራሉ ። በማንም አልፈርደም። ግነ እኮ ታወረ አልታወረ የእኔ ዕቃ ነው። የሚገርመኝ ‘ከውሮ’ ወደ ‘ጠንጋራ’ (ገና መባሌን ባልሰማ፣ እንዳማይቀር የማውቀው) አወዳደቄ ነው። የሚገርማችሁ ግን አያሳስበኝም። አዎ ቅር ይለኛል። ግን አሳስቦ፣ አሳዝኖ አያስተክዘኝም (አዳም፣ የወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ፤2003፣ ገፅ 225-226)።

… በቀስታ በቀስታ የተበላሸውን ዐይኔን መኳል ጀመርኩ። የሚያስፈራ ነገር አለው። ግን ይሄ አለመታደል እንደምታዩት ፊቴ ላይ የሰፈረውን ፈገግታ አያጠፋውም'' (አዳም፣ ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ፣ 2003፤ገፅ 226) ።

ሌላኛው እዚሁ ታሪክ ውስጥ የሚገኘ የኤግዚቴንሻሊዝም ፅንሰ-ሐሳብ የወንጀለኛነት ስሜት (guiltiness) ነው:: እንደ ሳርተር አመለካከት የወንጀለኘነት ስሜት የሚፈጠረው አንድ ግለብ በሚያደርጋቸው ማንኛቸውም ነገሮች ላይ ሙሉ ነፃነትና ሥልጣን እንዳለው መረዳቱና በዚህም ለሚፈፅማቸው ማንኛቸውም ድርጊቶች ኃላፊነቱ የግሉ መሆኑን ሲገነዘብ ነው:: በተመሳሳይመ መልኩ ገፀ-ባህሪዋ ላይ የተፈጠረው የጥፋተኘነትና የፀፀት ስሜት መነሻ በእሷ ፈቃደኘነት ጉድለት እጅግ ታፈቅረው ከነበረው ባሏ ልጅ ሳትወልድ እሱ ቀድሞ መሞቱና ለሞቱም ዋና መንስኤ መሆኗ ነው::

"… ልጅ ለመውለድ ከእኔ ይበልጥ እሱ ይፈልጋል:: ብዙ ጊዜ ባይሆንም ደጋግሞ መውለድ፣ ልጅ መልካም ነገር መሆኑን ያነሳሳል:: እኔ ግን ልጅ ማርገዝና ማጥባት አልፈለግኩም … እሱን ባሌን ብቻ ነበር የፈለኩት:: ከሁሉም ነገር እሱ ይበልጥብኝ ነበር (አዳም፣ አለንጋና ምስር ፤ 2004 ፤ ገፅ 253) ::

"… ያለፈውን ምሽት አስታወስኩ:: አሁን ባገኘው ተመኘሁ:: ይኼ ጊዜ ሳያልፍ እንዲያስረግዘኝ ፈለግኩ:: ውስጤን፣ ገንዳዬን በአምሳሉ እንዲሞላው ፈለግሁ:: አልመጣም:: ለዘላለም አልመጣም:: የተቀመጠበት ታክሲ ከአንድ አምቡላንስ ጋር ተጋጭቶ ነው አሉ:: ከአምቡላንስ ጋር ከሁለት ሰዓት በኋላ ሆስፒታል ተጠርቼ ሄድኩና ሲሞት አየሁት:: ጭንቅላቱን እየነቀነቀ … ለምን እንደነቀነቀ ይገባኛል:: እተጋደመበት ሕይወቱ ሲያልፍ … አንጀቴን አጥፌ ሆስፒታሉ ወለል ላይ እንደ አበደ ሰው ስፈራገጥ … “ዓለም ከአሁን በኋላ ትጥፋ”

ስል ለምወደው ባሌ ብቻ ያለቀስኩ የመሰላቸው ብዙ ነበሩ፡፡ ለእኔ እሱ ብቻ አልነበረም… መወደዴ ብቻ አልነበረም… አንድ የተመኘውን ነገር ላደርግለት ባለመፈለጌ ቆጭቶኝ ነው" (አዳም፣ አለንጋና ምስር ፣ 2004 ፣ ገፅ 257-258 )፡፡

"… ያን ዕለት ማታ "እሺ" ብለው ኖሮ፣ በሰላም እናድር ነበር፤ በሰላም ብናድር ኖሮ በሰላም ጠዋቱን አብረን እናረፍድ ነበር … ታክሲ የለ አምቡላንስ ያለ፡፡ አሁን እዚህ ተቀምጬ እንዳሻቸው በሚሆኑ አበቦች እቀናለሁ … በለውጥ በሚንቦገቦጉ፡፡ እኔ ግን በበቀል ለምለም ማህፀኔን እያጠወለግሁ … እግዜር ያበጀለት መረቁን በቁጭትና በተስፋ መቁረጥ በየቦታው እያዝረበረብኩ" (አዳም ፣አለንጋና ምስር፣ 2004፣ ገፅ 259) ፡፡

"… ገላየ በጊዜ ብዛት እየወፈረ … የመነኮሰ ጭኔ ብቻውን እያደገ፣ የወር አበባዬ እየመጣ ሲጠፋ፣ ጡቴ እየወደቀ፣ የሆዴ ቦርጭ እየገፋ … ሽንጤ እያጠረ ሲሄድ አያለሁ፡፡ መታጠቢያ ቤት መስታወት ፊት ለፊት ቆሜ የብቸኘነት አወዳደቄን ሳይ፣ ወተት ሳይወርደኝ፣ የዕንግዴ ልጅ ሳይጠረገኝ፣ ማህፀኔ ሳይቆስል፣ ለአንድ ለምወደው ሰው ይኼን ሁሉ የማየውን ሥጋና ደም ሥር ሳልሰጠው መቅረቴ አንጀቴን ይበላኝና ከቆምኩበት ወድቄ መሬት በጥፊ እየመታሁ አለቅሳለሁ፡፡ በጥፊ እየመታሁ፡፡ ይኼ ሁሉ ስቃይ ግን ከእግዜርና ከሰይጣን በስተቀር ማንም ሳያውቀው ባዶ ቤት ውስጥ ይቀራል እየመሰለኝ"
(አዳም፣ አለንጋና ምስር፣ 2004፣ገፅ 260) ፡፡